**ስለታገቱት ተማሪዎቹ መታገት ቅጥ ያጣው እና ትልቅ የውጪ ድምጽ አጥቶ የነበረውን መንገድ እንዲይዝ አድርጌለሁ።**

ለዚህ ምስጋናዬ ለአለም ፈጣሪ ለእየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለታገቱት የደምቢዶሎ ዩንቨርስቶ ተማሪዎች አምነስቲ ኢንተርናሽናል እውቅና ሰጥቶት ተማሪዎቹ መታገታቸውን እንዳይመዘግብ እና ድምጻቸው እንዳይሆን ያደረገውን ድብቅ ኃይል በአምላክ ፍቃድ እና ኃይል የተማሪዎቹ እና የቤተሰቦቻቸው እንባን ጠራጊው ፡ ግቤን እንድመታ ስላደረገው ለተመደው ደግነቱ በድጋሜ በተደጋጋሚ ምስጋና ይግባው። በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ አንድነት ሬድዮ አዘጋጅ እና አቅራቢ አቶ ተኮላ ወርቁን ፡ ስለተማሪዎቹ እሱም እንቅልፍ ስለነሳው ጉዳዩ በጣም ትልቅ ጥረት ቀን በቀን የሚጠይቅ ስለነበረ እራሱ አስቦ እየደወለልኝ ከስውዲን ሲያበረታታኝ ስለነበረ እድሜ እና ጤና ከእነ ቤተሰቡ መድሃኔዓለም እየሱስ ክርስቶስ ያብዛለት። የኢትዮፓትሪዎትስ ድህረገጽ መስራች እና ባለቤት ኤዲተር እና አድሚን አቶ ይትባረክ ሃይሉ ወንድም አገኝን ስላደረገልኝ ትልቅ የወንድምነት አይዞሽነት ድጋፍ በጣም አመሰግናለሁ። ለሱም እድሜ ከጤና ጋር ክርስቶስ ያብዛለት ከእነመላው ቤተሰቡ። ሆነ ተብሎ የተባበረ መኖሩን ካረጋገጥኩኝ በኋላ ትልቅ ትግል በብዙ መልኩ ማድረግ ነበረብኝ። በበኩሌ በብዙ ትግል ፡ የታገቱት የደንቢዶሎ ተማሪዎች ጉዳይ እውቅና እንዳያገኝ በአምነስቲ ኢንተርናሽናልበ በኩል ትልቅ ቀጥተኛ እና ውጣ ውረድ ያለው ትግል በማድረግ ችግሩ የት እንደሆነ አስደርጌለሁ። በፌስ ቡክ ላይ ያሉት ለኢትዮጵያ እና ለሕቧ እናም ለታገቱት ተማሪዎች ነጋ ጠባ በሜሴንጀር ጭምር ጉዳዩን እንድበረታበት በጣም በጣም ትልቅ ሞራል ለሰጡኝ ሁሉ ትልቅ ምስጋና አቀርባለሁ። ትግሉ ይቀጥላል ተማሪዎቹ እስኪፈቱ እና በይፋ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለቤተሰቦቻቸው ሲያስረክባቸው እስከናይ ድረስ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።

የኢትዮጵያወርቅ (የሐረርወርቅ) ጋሻው
ዘብሄረ አንዲት ኢትዮጵያ።